# ተደጋጋሚ ውሸት ሃቅን ሊወልድ አይችልም!

**መላኩ በቀለ 03/16/14**

የኢፌዴሪ መንግስት እያከናወናቸው የሚገኙ ሁሉም የልማት ተግባራት የሀገሪቱን ሕገ-መንግሥት መነሻ ያደረጉ ናቸው፡፡ በሕገ- መንግስቱ አንቀጽ ስምንት ተራ ቁጥር አንድ ላይ የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች የሀገሪቱ ሉዓላዊ ሥልጣን ባለቤቶች መሆናቸው በመደንገጉ፤ የሀገሪቱን ሀብት በእኩልነት የመጠቀም መብታቸው ሊረጋገጥ ችሏል፡፡ ከዚህ አኳያ መንግስት በማያቋርጥ ዕድገት የህዝቡን ኑሮ ለማሻሻል የሚያስችሉ ፖሊሲዎችንና ስትራተጂዎችን በመንደፍ ዜጎች የምጣኔ-ሀብትና ማህበራዊ ልማቶች ተጠቃሚ እንዲሆኑ በትጋት በመስራት ላይ ይገኛል፡፡

በመሆኑም መንግስት በመላው ሀገሪቱ የሚያከናውናቸውን በርካታ ፕሮጀክቶችን በየክልሉ ተግባራዊ ሲያደርግም ለአካባቢው ነዋሪዎች ሁለንተናዊ ተጠቃሚነት የቅድሚያ ትኩረት ከመስጠቱም በላይ፤ የሀገሪቱ ታሪካዊ፣ ተፈጥሯዊ፣ ባሕላዊ እና ሃይማኖታዊ ቅርሶች እንደተጠበቁ የሚቆዩበትን አቅጣጫ ጭምር ይከተላል፡፡ ዳሩ ግን የህዝብን ኑሮ መሻሻል የማይፈልጉና ለራሳቸው ጥቅም ብቻ የቆሙ ፀረ ልማት ኃይሎች፤ ይህ አካሄድ "የዳቦ ኮሮጆአቸውን" ስለሚጎዳ አይፈልጉትም። ከዚህ በመነሳትም ቀንና ማታ በተለያዩ ስያሜዎች ራሳቸውን እየቀያየሩ በመደጋገም የመንግስት ስም ጥላሸት ለመቀባት ሲሯሯጡ ይስተዋላሉ–አንዳንዴ በተናጠል፣ ሌላ ጊዜ ደግሞ በጣምራ እየሆኑ።

ለዚህ አባባሌ መነሻ የሆነኝ ከመሰንበቻው ፀረ-ኢትዮጵያ ተቋሙ ሂዩማን ራይትስ ዎችና ተጣማሪው ኢንተርናሽናል ሪቨርስ የተሰኘ አክራሪ ኒዩ-ሊበራል ድርጅት በጋራ የሰጡት መግለጫ ነው። ለወትሮው በተደጋጋሚ ሁለት ጊዜ ተመሳሳይ አሉባልታዎችን በማናፈስ የሚታወቁት እነዚህ ተቋማት፤ የሀገራችንን "ከአንድ ብርቱ፣ ሁለት መድሃኒቱ" የሚለውን ብሂል ወደ "ከአንድ ከንቱ፣ ሁለት ገልቱ" ቀይረውት በሚመስል ሁኔታ የተለመደውን ማላዘናቸውን አሰምተውናል–'የኢትዮጵያ መንግስት በደቡብ ኦሞ በማስገንባት ላለው የስኳር ፋብሪካ የመንገድ ግንባታ የቦዲ ብሔረሰብ መሬት ሙሉ ለሙሉ እንዲጠረግ አድርጓል እንዲሁም በጊቤ ወንዝ ላይ በሚያካሂደው የኤሌክትሪክ ሃይል ማመንጫ ግድብ (ጊቤ ሶስት) ግንባታ ሳቢያ አካባቢው ክፉኛ እየተጎዳ ነው' በማለት።

አክራሪ ኒዩ-ሊበራል ተቋማቱ መሬት ላይ ያሉትን ዕውነታዎች ከመጤፍ ሳይቆጥሩ የተሰለቸውን እንዲሁም እንደ ሐምሌና ነሐሴ ዝናብ የማያባራ ድርሰታቸውን ይዘው ብቅ ያሉት፤ ምናልባትም "ውሸት ሲደጋገም እውነት ይመስላል" የሚል ያረጀ ያፈጀን ብሂል ይዘው እያቀነቀኑ ሊሆን ይችላል። ግና ተደጋጋሚ ውሸት ሃቅን ሊወልድ እንደማይችል ሊያውቁት የሚገባ ይመስለኛል። ምክንያቱም ሐሰት አርባ ክንድ ቢዘረጋ አንድ ስንዝር እውነት እንኳን ሊወጣው ስለማይችል ነው።

በመሆኑም ከዚህ አኳያ ለድርጅቶቹ ፍብረካ እንደ ማንኛውም ዜጋ አግባብ ያለው ምላሽ መስጠት ተገቢ ነው ብዬ አምናለሁ—"አካፋን አካፋ" ማለት ስለ ሀገሩ ልማት ከሚያስብ ዜጋ የሚጠበቅ ተግባር ነውና።...እናም እነዚህ የርዕዮተ-ዓለም ግብን እንጂ፣ የሰብዓዊ መብትንም ይሁን የአካባቢ ጥበቃ ስራዎችን በፍፁም የማይወክሉ ፅንፈኛ ሃይሎች ወደ ፈጠሩት ተደጋጋሚ ውትወታዎች አፅመ-ታሪክ ልውሰዳችሁ።...

ከእኛ ወዲያ ለእኛ ለማሰብ የሚዳዳቸው እነዚህ "የፖለቲካ ዳቦ ጋጋሪዎች"፤ የኢትዮጵያ መንግስት በደቡብ ኦሞ የሚያካሂደው የግድብ ግንባታ፣ የሸንኮራ አገዳ ልማትና በሰፋፊ መሬቶች ላይ በሚካሄድ የንግድ ግብርና ሳቢያ ከሃምሳ ሺህ በላይ በሚሆኑ በአካባቢው አርብቶ አደሮች ላይ ከፍተኛ አደጋ ያስከትላል። በስኳር ልማት ምክንያት በአካባቢው ለዘመናት ይኖሩ የነበሩ የቦዲ ብሔረሰብ አባላትን ሳያማክርና አስፈላጊውን ካሳ ሳይከፍል መሬታቸውን በቡልዶዘር መጥረጉን የሚያሳይ የሳተላይት ምስል አግኝተናል ባይ ናቸው። እርግጥ እነዚህ የተቋማቱ የተለመዱና ምናልባትም በአዲስ መልክ የታከለውና 'በሳተላይት ጭምር ሰልለናችሁ ሃቁን አረጋግጠናል' በማለት ያሰፈሩት ዕውነታ ውሃ የማይቋጥር መሆኑን ለመገንዘብ አያዳግትም።

የኢፌዴሪ መንግሥት በ2003 ዓ.ም የነደፈው የአምስት ዓመት የዕድገትና የትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ሀገሪቱ ለመልማት ያላትን ዕምቅ አቅም በእጅጉ በማገናዘብ ዜጎች ከሚገኙት የልማት ትሩፋቶች በየደረጃው በሚገባ እንዲጠቀሙ በማሰብ የሚከናወን ነው፡፡ ይህ ዕቅድ በተግባር ላይ ከመዋሉ በፊትም መንግስት ከየአካባቢው ነዋሪዎች ጋር በሚገባ በመወያየት ብሎም ነዋሪው ልማቱ የራሱ መሆኑን ካመነ በኋላ ስራው የሚጀመር መሆኑ ከማንም የተሰወረ ጉዳይ አይደለም። እናም አክራሪ ኒዮ-ሊበራል ተቋማቱ ባህር ማዶ ተቀምጠው እንደሚያስወሩት ሳይሆን፣ እዚህ ሀገር ውስጥ ህዝብ ሳያምንበትና ስራውን በየኔነት ስሜት ለመተግበር ሳይስማማ የሚከናወን አንዳችም ጉዳይ የለም። በደቡብ ኦሞ

ከባቢ የሚኖሩት የሸንኮራ አገዳም ይሁን የግድብ ልማት ፕሮጀክቶች ከዚህ ሀገራዊ አሰራር የተለየ ሊሆኑ የሚችሉበት ምንም ዓይነት ምክንያት የለም። የየትኛውም ልማታዊ ተግባር ግንባር ቀደም ተዋናይ በየአካባቢው የሚገኘው ህዝብ እንደመሆኑ መጠን፣ ይህን ታላቅ ሃይል ከግምት ውስጥ ሳያስገባ የሚከናወን የዕድገት ትልም ውጤት ሊያስገኝ ስለማይችል ነው።

በሀገር አቀፍ ደረጃ የተካሄደ አንድ ጥናት እንደሚያመለክተው፤ ሀገራችን ከ500 ሺህ ሄክታር የሚበልጥ መሬቷን ለሸንኮራ አገዳ ልማት ማዋል ትችላለች፡፡ ሀገራችን የተቸራት ለስኳር ልማት ዘርፍ ምቹ የሆነ መሬት ብቻ ሳይሆን፣ በጥናት በተረጋገጡ አካባቢዎች ለሸንኮራ አገዳ ልማት ስራው በእጅጉ የሚያስፈልገው ውኃም በበቂ ሁኔታ መኖሩ ጭምር ነው፡፡ ይህ ብቻ አይደለም። የአካባቢዎቹ የአየር ንብረት ሁኔታም ለዘርፉ ልማት ተስማሚ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ በመሆኑም ይህንን ዕምቅ ሃብት አቅምን አሟጦ መጠቀም የሚያስችል የልማት ስትራቴጂን ተነድፎና ከህዝቡ ጋር ምክክር ተደርጎ ወደ ስራው ለመግባት ተችሏል፡፡

እንደሚታወቀው መንግሥት ሀገራችንን መካከለኛ ገቢ ካላቸው ሀገሮች ተርታ ሊያሰልፏት ይችላሉ ብሎ ከተለማቸው የልማት ዘርፎች መካከል የስኳር ልማት ዘርፍ አንዱ ነው፡፡ በዚህም ሀገሪቱ በልማት ዕቅዱ ዓመታት ውስጥ እየገነባች በምትገኘውና በምትገነባቸው አስር አዳዲስ ስኳር ፋብሪካዎች እንዲሁም በነባር ስኳር ፋብሪካዎች በተካሄዱ የማስፋፊያ ስራዎች እና የመጀመሪያ ምዕራፍ ሥራው በማጠናቀቂያ ሂደት ላይ በሚገኘው ግዙፉ የተንዳሆ የስኳር ፋብሪካ አማካኝነት ግብ ጥሏል። በዕቅዱ መጨረሻ ላይ በዘርፉ ሊደረስበት በታቀደው ግብ መሰረትም ኢትዮጵያ ከውጭ ለምታስገባው ስኳር፣ ቤንዚን፣ ኬሮሲን… ወዘተ. ይወጣ የነበረን የውጭ ምንዛሬ በእጅጉ ማስቀረትና መቀነስ እንደሚቻል ይታመናል፡፡ ከዚህም አልፎ ስኳርን ወደ ውጭ በመላክ ለሀገሪቱ የውጭ ምንዛሬ ገቢ ማስገኘት ስለሚቻል መንግሥት ለዘርፉ ትልቅ ትኩረት ሰጥቶ እየሰራ ይገኛል፡፡

ዘርፉ ለሀገሪቱ ዜጎች ሰፊ የስራ ዕድል በመፍጠር ረገድ የሚኖረው ፋይዳም ቀላል አይደለም። ይህም የፀረ-ድህነት ትግሉን በመደገፍ ረገድ ዓይነተኛ ሚና ይጫወታል፡፡ በመገንባት ላይ ካሉት የስኳር ፋብሪካዎች የሚገኝ የኤሌክትሪክ ኃይል ሌላው በዘርፉ ከሚደረግ የልማት እንቅስቃሴ የሚገኝ ትሩፋት ሲሆን፤ ይህም ሀገራችን ኢንዱስትሪ መር ምጣኔ-ሃብት ለመገንባት እያካሄደችው ላለው የኢኮኖሚ ዕድገት አቅጣጫ ትልቅ ፋይዳ

እንደሚኖረው አያጠያይቅም፡፡ በመሆኑም የስኳር ልማት ዘርፍ ሀገራችን ከድህነት ለመውጣት እያደረገችው ላለው ትግል ጉልህ ሚና የሚጫወት እና መንግሥት በቁርጠኝነት የዘመተበት ለድርድር የማይቀርብ የልማት ትልም እንደሆነ አክራሪ ኒዮ-ሊበራል ተቋማቱ ሊያውቁት የሚገባ ይመስለኛል፡፡ ምክንያቱም ጉዳዩ እነርሱ ለራሳቸው ‘የዕለት እንጀራ’ ሲሉ ብቻ እንደሚመለከቱት ሳይሆን፤ ለሀገራችን ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች የሞትና የሽረት እንዲሁም የህልውና ጉዳይ ስለሆነ ነው።

የዚህን ፅሑፍ አቅራቢ እጅግ ያስገረመኝ ጉዳይ ቢኖር፤ አክራሪ ኒዮ-ሊበራል ተቋማቱ መንግስት እንደምን ህዝቡን ሳያማክር የልማት ፕሮግራሞቹን ማከናወኑን በሳተላይት እንደተመለከቱ ነው። ተቋማቱ እንዲያው ለወሬ ያህል የቦዲ ነባር የአካባቢው ማህበረሰብ አባላት መሬት ሙሉ ለሙሉ ለስኳር ፋብሪካው ግንባታ ሲባል ሲጠረግ ተመልክተናል ቢሉ እንኳን፤ እንዴት ነው መንግስት ከአካባቢው ማህበረሰብ ጋር መመካከርና አለመማከሩን በሳተላይት ሊመለከቱ የሚችሉት?...አናንተዬ ኧረ ለመሆኑ ምን ዓይነት ዓይን ያወጣ ቅጥፈት ነው እየተከናወነ ያለው?...ጉዳዮ ውሸት ቢሆንም እነዚህ ድርጅቶች ለምንድነው የኢትዮጵያ ህዝቦችን የልማት ስራ በሳተላይት የሚሰልሉት?...እንዲህ የማድረግስ ምን ዓይነት ህጋዊ መብት አላቸው?...እርግጥ ለእነዚህ ሁሉ ጥያቄዎች ምላሹ ግልፅ መሆኑን ውድ አንባቢዎቼ እንደምትገነዘቡት ተስፋ አደርጋለሁ። ምክንያቱም ከዚህ ሁሉ የቅጥፈት ክምር በስተጀርባ ያለው ሃቅ የአደባባይ ምስጢር ነውና—ሀገራችን በራሷ የልማት አቅጣጫና ትልም እንዳታድግ የሚደረግ የፅንፈኛ ኒዮ-ሊበራል ሃይሎች ርብርብ መሆኑ።

ለነገሩ ተቋማቱ አፍሪካን ብሎም በፈጣን ዕድገቷ የምትታወቀውንና “አፍሪካዊቷ ነብር” ለመባል የበቃችው ሀገራችን በራሷ የልማት መንገድና የፖለቲካ ዘይቤ እንድታድግ የሚፈቅዱ ኃይሎች አይደሉም፡፡ ይህ እሳቤያቸውም በየትኛውም አፍሪካዊ ሀገር ላይ ያለምንም መሸራረፍ እንዲሰራ ይፈልጋሉ፡፡ ታዲያ ይህን “የመከነ ፖለቲካቸውን” ተፈጻሚ ለማድረግ ለራሳቸው “ለትርፍ ያልተቋቋመ” የሚል ስያሜ በመስጠት በተለያዩ ምግባረ ሰናይና ሲቪክ ማህበራት የሽፋን ስም ይደራጁና የሀገራቱን ልማት ለማደናቀፍ የማይቧጥጡት ዳገት፣ የማይቆፍሩት ጉድጓድ፣ የማይወረውሩት የአሉባልታ ድንጋይ የለም።

ይህን ለመተግበርም በየሀገራቱ ውስጥ ትላልቅ ተቋማትን ከመጠቀም ጀምሮ የቀለም አብዮትን እስከ ማቀጣጠል ድረስ ይደርሳሉ፡፡ በእኛ ሀገር ነባራዊ ሁኔታ ግን የቀለም አብዮት የሚካሄድበት ምንም ዓይነት ተጫባጭ ምህዳር ባለመኖሩ፤ የቁራ ጩኸታቸውን

የሚሰማቸው ሲያጡ አማራጫቸውን “ውሸትን ብንደጋግም እውነት ይመስልልናል” የሚል አሮጌ ይትብሃል ማድረጋቸውን ለመገንዘብ አይከብድም፡፡

ማንኛውም የዚህ ፅሑፍ አንባቢ እንደሚያውቀው “ለህዝቦች ሰብዓዊ መብት እንሟገታለን፣ የወንዞች ጉዳይ ይመለከተናል፣ ግጭቶችን እንፈታለን…ወዘተ” በሚል የሽፋን ስም ተደራጁት እንደ ሂዮማን ራይትስ ዎች፣ ኢንተርናሽናል ሪቨርስና ኢንተርናሽናል ክራይስስ ግሩፕ…ወዘተ. የመሳሰሉት ተቋማት፤ በማደግ ላይ ያሉ ሀገራት ዕድገታቸውን በተገቢው ደረጃ ካረጋገጡ እነርሱ በሽፋንነት የተደራጁበት ሚናቸው ተፈላጊ እንደማይሆን ጠንቅቀው ይገነዘቡታል፡፡ ምክንያቱም ሀገራቱ የተፈጥሮ ፀጋዎቻቸውን በተገቢ ሁኔታ ተጠቅመው የዕድገት ማማን በከፍተኛ ደረጃ መቆናጠጥ ከጀመሩ፤ እንከራከርለታለን የሚሉት ሰብዓዊ መብት፣ እንፈታቸዋለን የሚሏቸው ግጭቶች ወዘተ. ከዕድገቱ ጋር ተያይዘው ችግርነታቸው ታሪክ ስለሚሆን፤ የተከናነቡት የውሸት ጭምብል መገፈፉ ስለማይቀር ነው፡፡ ይህም ከድብቅ የፖለቲካ አጀንዳቸው ባሻገር፤ በሰብዓዊ መብትና በግጭቶች ሰበብ ቀደም ሲል ወደ ኪሳቸው ይገባ የነበረው ረብጣ ዶላር እንዳይኖር ስለሚያደርግ ጥቅማቸውን ክፉኛ ያጎዳዋል፡፡

በመሆኑም በደቡብ ኦሞ አካባቢ የሚከናወኑ የልማት ስራዎች ሳቢያ ኢትዮጵያዊኑ የዘመናት ድሃዎች ከኩራዝ ኑሮ ወጥተው የኤሌክትሪክ ኃይል ተጠቃሚ መሆናቸው አይቀርም፡፡ ይህም የአካባቢው ህዝቦች በመሰረተ - ልማትና በሌሎች መሰረታዊ አገልግሎቶች ሳቢያ ዓይናቸውን በመክፈት የአኗኗር ዘይቤያቸውን እንዲቀይሩ ያደርጋቸዋል፡፡ ህይወትን ከዚህ በፊት ከነበረው በተለየ ሁኔታም መምራት ይጀምራሉ፡፡ የወንዞችንና የሰብዓዊ መብት ጥቅምን እንዲሁም የግጭት አላስፈላጊነትን ስለሚገነዘቡም ቀደም ሲል በግጦሽና በውኃ ምክንያት ከሚጋጯቸው ህዝቦች ጋር በሠላም ተከባብረው ይኖራሉ፡፡ ታዲያ አንድ ህዝብ ከዕድገት ጋር ተያይዞ በሚፈጥረው ሚዛናዊ እሳቤ ስለ የተፈጥሮ ፀጋ ጠቀሜታ፣ ስለ ሰብዓዊ መብትም ይሁን ስለ ግጭት አፈታት በቂ ግንዛቤ ከያዘ ፤ በእነዚህ ጉዳዩች ላይ እንሟገታለን የሚሉ ድርጅቶች አያስፈልጉም፡፡ ከልማቱ ጋር በሚዳብር ንቃተ - ህሊና የተመቻቸ አካባቢና የቅርስ ጥበቃ አስተሳሰብ መጎልበቱ ስለማይቀር፤ የአካባቢ ተንከባካቢ ድርጅትም ተፈላጊነት የለውም፡፡

በዚህም ሳቢያ በደቡብ ኦሞ የሚከናወነው ልማት አደጋው ከአካባቢው ህዝቦችና ስነ-ምህዳር ይልቅ ለአክራሪ ኒዮ- ሊበራል ተቋሞች ይሆናል ማለት ነው፡፡ ልማቱ ሁሉንም የአካባቢውን

ማህበረሰብ ይጠቅማል እንጂ አክራሪ ኒዮ-ሊበራል ሃይሎቹ እንደሚያስወሩት ከ50 ሺህ በላይ ዜጎችን አያፈናቅልም። ይልቁንም ሊፈናቀሉ የሚችሉት ለዳቦአቸው ሲሉ የውሸት ሪፖርት ጋጋታ ማቅረብንና በአሳፋሪ ሁኔታ አንዲት ሉዓላዊ ሀገርን መሰለል ስራዬ ብለው የተያያዙት ፅንፈኛ ሃይሎች ናቸው። እናም የደቡብ ኦሞ የስኳርም ይሁን የግድብ ግንባታ ልማት ሊያፈናቅል የሚችለው፤ ውሸት ካላወሩ ቤሳ ቤስቲ ደመወዝ ሊያገኙ የማይችሉ የፖለቲካ ነጋዴዎችን ብቻ መሆኑ ሊታወቅ ይገባል ባይ ነኝ።

እርግጥ እነዚህ ሆድ-አደር አክራሪ ኒዮ-ሊበራል ሃይሎች ይሉኝታ አሊያም ግብረ ገብነት አላቸው ብሎ የሚያስብ የዚህ ፅሑፍ አንባቢ ካለ እውነትም እንደ እኔ መሳሳቱ የሚቀር አይመስለኝም—ተቋማቱ ሃፍረተ-ቢሶች ናቸውና። አዎ! ይህ ማንነታቸው በዚህኛው የወሬ ዲስኩራቸው ላይም በገሃድ ተንፀባርቋል። ተቋማቱ ለዳቦአቸው ሲሉ ያለ አንዳች ሃፍረት የመንግስታቱ ድርጅት ኢትዮጵያን ጨምሮ ሌሎች በማደግ ላይ በሚገኙ ሀገሮች ውስጥ እንዲመጣ ግብ አስቀምጦ የሚንቀሳቀስለት ልማትን እንድናቆም ጭምር ከማስጠንቀቅ ወዳ ኋላ አላለሉም። እናም እንዲህ ብለዋል–“የኢትዮጵያ መንግስት የስኳር ልማቱን በአፋጣኝ በማቆም፤ የአካባቢውን ህዝቦች በቅጡ ሊያማክርና የሚያደርሰውን ተፅዕኖ በሰለጠኑ ባለሙያዎች ሊያስጠና ይገባል።”…መቼም ወደው አይስቁ እንጂ ሌላ ምን ይባላል?!...

ለነገሩ ‘ልማትን አቁሙ’ የሚል የሰብዓዊ መብትና የአካባቢ ጥበቃ ምን ዓይነት እንደሆነ የሚያውቁት እነዚህ አስገራሚ አክራሪዎች ቢሆኑም፤ እኔ እስከሚገባኝ ድረስ ግን አንድን በማደግ ላይ የሚገኝ ሀገር ልማትህን አቁም ማለት የህዝቡን የማደግና ከድህነት የመውጣት የማይገሰስ መብትን በይፋ መንጠቅ እንጂ መጠበቅ አይደለም። ግልፅ ነጠቃ እንጂ ጥበቃ ሊሆንም አይችልም። ያም ሆነ ይህ ግን በደቡብ ኦሞ እየተካሄደ ያለው የስኳር ፕሮጀክት ተጨባጭ ዕውነታዎች የእነዚህን ሃይሎች የቅጥፈት ካባ ዕርቃኑን ስለሚያስቀረው ወደዚያው ማምራቱ ተገቢ ይመስለኛል።…

በቅርቡ በጉዳዩ ዙሪያ የወጣ አንድ መረጃ እንደሚያመለክተው፤ ኢትዮጵያ ካሏት ለስኳር ልማት ተስማሚ ከሆኑ አካባቢዎችና የልማት ቀጣናዎች መካከል በደቡብ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልላዊ መንግሥት ስር የሚገኙት ከደቡብ ኦሞ ዞን የሰላማጎ እና የኛንጋቶም ወረዳዎች፣ ከቤንች ማጂ ዞን ማጂ፣ ሱርማ እና ሜኢኒትሻሻ ወረዳዎች እንዲሁም ከካፋ ዞን የዴቻ ወረዳ የተመረጡ አካባቢዎች በተለያየ ሁኔታ ለስኳር ልማት ዘርፍ ሰፊ ዕምቅ አቅም አላቸው፡፡ ይህ በ‘ኩራዝ ስኳር ልማት ፕሮጀክት’ ስም በተጠቀሱት

አካባቢዎች የሚካሄደው ልማት፤ ሀገራችን በዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅዱ ወዳስቀመጠቻቸው ግቦች ለመድረስ የሚጫወተው ሚና እጅግ ከፍተኛ መሆኑም በጥናት ተረጋግጧል፡፡

በመሆኑም መንግስት በፕሮጀክቱ አማካኝነት አምስት ስኳር ፋብሪካዎችን (ሦስቱ በቀን 12 ሺህ ቶን፣ ሁለቱ ደግሞ በቀን 24 ሺህ ቶን አገዳ መፍጨት የሚችሉ) ለመገንባትና የኦሞ ወንዝን በመጠቀም በ175 ሺህ ሄክታር መሬት ላይ የሸንኮራ አገዳ ልማት ለማካሄድ ሲንቀሳቀስ አካባቢው ለዘርፉ ልማት ያለውን ሰፊ ዕምቅ አቅም አገናዝቦ መሆኑ ሊታወቅ ይገባል፡፡ በፕሮጀክቱ የሚተከሉት ፋብሪካዎች በጠቅላላው በዓመት አንድ ሚሊዮን 946 ሺህ ቶን ስኳር የማምረት አቅም ይኖራቸዋል። በእነዚህ ፋብሪካዎች አማካኝነትም ዋና እና መለስተኛ ከተሞች የሚመሰረቱ ሲሆን፤ ስምንት የእርሻ መንደሮች እና ከ20ሺህ በላይ መኖሪያና መኖሪያ ያልሆኑ ቤቶች እንዲሁም የመሰረተ ልማት አውታሮችና የማህበራዊ አገልግሎት መስጫ ተቋማት ይገነባሉ፡፡

በፕሮጀክቱ ይዞታ ውስጥም ሆነ ውጭ በሆኑ አካባቢዎች የሚኖረውና ሰፊ ቁጥር ያለው ህዝብ በአርብቶ አደርነት የሚኖርና በተለይ ለከብቶቹ እና ለእራሱ ውኃ ፍለጋ ከቦታ ቦታ የሚንከራተት ከመሆኑም በላይ፤ አካባቢዎቹ በዝናብ ውኃ ዕጥረት ሳቢያ በተደጋጋሚ ለድርቅ የሚጋለጡም ናቸው፡፡ በአካባቢዎቹ ወራጅ ውኃን ተከትሎ በጣም ጥቂት በሆኑ ቦታዎች ውስን የእርሻ ስራ ከመካሄዱ በስተቀር ይህ ነው የሚባል የሰብል ምርት አይስተዋልም። በእነዚህ አካባቢዎች በእርሻ ስራ ተሰማርቶ የሚገኝ የህብረተስብ ክፍል ቁጥር እጅግ ዝቅተኛ ደረጃ ላይ ይገኛል፡፡ ህዝቡ እንደ ትምህርት ቤት፣ ጤና ጣቢያ፣ ንጹህ የመጠጥ ውኃ፣ መንገድ፣ የወፍጮ አገልግሎት እና ከመሳሰሉት ማህበራዊ እና የመሰረተ ልማት ተቋማት ጋር የማይተዋወቅና በድህነት ቀንበር ኑሮውን እንዲገፋ ተገዶ ለዘመናት ወደዳር ተገፍቶ የኖረ ነው፡፡

በደቡብ ኦሞ ዞን የምትገኘውና በአሁኑ ወቅት የስኳር ልማት እንቅስቃሴው የተጀመረባት የሰላማጎ ወረዳ ብቻ ናት። በወረዳዋ ሶስት ቀበሌዎች ብቻ ይገኛሉ፡፡ አክራሪ ኒዮ-ሊበራል ሃይሎቹ የጠቀሱት ቦዲ እንዲሁም ሙርሲ፣ ባጫና ዲሜ ብሔረሰቦች በተበታተነ ሁኔታ በሚኖሩባት በዚች ወረዳ፤ የዲሜ ብሔረሰብ ተወላጆች ብቻ በእርሻ ሥራ የሚተዳደሩ ሲሆኑ አብዛኛውና ቀሪው የወረዳዋ ነዋሪ ብሔረሰቦች አርብቶ አደሮች ናቸው፡፡ በመሆኑም በስኳር ልማቱ ሳቢያ የሚፈናቀል የለም፡፡ በወረዳዋ ልማቱ በተጀመረበት አካባቢም ሆነ

በዙሪያዋ የሚገኙ አካባቢዎች ከዚህ ቀደም ከምንም ዓይነት የመሠረተ ልማት አውታሮችና የማህበራዊ አገልግሎት መስጫ ተቋማት ጋር አይተዋወቁም ነበር፡፡ ዛሬ ግን ከልማቱ ጋር ተያይዞ በአካባቢው የሚገኙ የህብረተሰቡ ክፍሎች የመሰረተ ልማት አውታሮችና የተለያዩ ማህበራዊ አገልግሎት መስጫ ተቋማት ተጠቃሚ መሆን ጀምረዋል፡፡ ይህም የልማት ስራው ትሩፋት እንጂ የሀገራችንን ዕድገት ለማየት የማይሹ ሃይሎች እንደሚዋሹት የስኳር ፕሮጀክቱ ለአካባቢው ህዝብ አደጋ አለመሆኑን የሚያሳይ ነው።

አክራሪ ኒዮ-ሊበራል ተቋማቱ እንደሚያስወሩት ሳይሆን፣ የፌደራልና የክልል መንግሥታት የስኳር ልማት እንቅስቃሴው ከመጀመሩ በፊትም ይሁን በኋላ ከህዝቡ ጋር በአካል ተገናኝተው በልማቱ ዙሪያ በተደጋጋሚ ተወያይተዋል፡፡ በዚህ መልክ ነበር የየአካባቢዎቹ ሕዝብ በልማቱ ካመነና ተጠቃሚ እንደሚሆን ሙሉ በሙሉ ከተረጋገጠ በኋላ ተግባራዊ እንቅስቃሴዎች የተጀመሩት፡፡ መንግስትና የልማት ስራውን የሚያከናውነው ስኳር ኮርፖሬሽን የኩራዝ ስኳር ልማት ፕሮጀክትን እንቅስቃሴ ሲጀምር የቅድሚያ ትኩረት በመስጠት የተንቀሳቀሱት እጅግ ኋላቀር በሆነ የአኗኗር ሁኔታ ኑሮውን እየገፋ የሚገኘውን የወረዳዋን አርብቶ አደር ሕዝብ የመሠረተ ልማት እና የማህበራዊ አገልግሎት መስጫ ተቋማት እጦት በመፍታቱ ተግባር ላይ ነው፡፡

መንግስት ወደ ልማት ስራው የገባውም የሰላማጎ ወረዳ አርብቶ አደር በፈቃደኝነት ላይ ተመስርቶ በመንደር እንዲሰባሰብ በማድረግ ሲሆን፣ አርብቶ አደሩ በጥልቅ የውሃ ጉድጓድ ቁፍሮ አማካይነት የንፁህ መጠጥ ውኃ አቅርቦት እንዲያገኝ፣ እህል በእጅ ፈጭቶ መመገብ የለመደው ሕዝብ የወፍጮ አገልግሎት ተጠቃሚ እንዲሆን፣ ለራሱም ሆነ ለከብቶቹ በአቅራቢያው የሕክምና አገልግሎት እንዲያገኝ፣የአርብቶ አደሮች ማሰልጠኛ ተቋም በመገንባትና የአርብቶ አደሩ ልጆች የትምህርት አገልግሎት እንዲያገኙ የሚቻልበትን ሁኔታ አስቀድሞ በማመቻቸት መሆኑን መረጃዎች ያስረዳሉ፡፡ በዚህም የአንደኛ ደረጃ የመጀመሪያና ሁለተኛ ሳይክል ትምህርት ቤቶች፣ የሰውና የእንስሳት ጤና ኬላዎች፣ የአርብቶ አደር ማሰልጠኛ ጣቢያዎች፣ የቀበሌ ጽሕፈት ቤቶች፣ የኮሙዩኒቲ ፖሊሲንግ ጽሕፈት ቤቶች፣የግብርና እና የጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያዎች መኖሪያ ቤቶች፣ የመንገድ አውታሮች ተገንብተው አገልግሎት እየሰጡ ይገኛሉ፡፡

ከዚህ በተጨማሪም የአካባቢውን ተወላጆች ወደ ከፊል አርሶ አደር ለመቀየር በመስኖ የሚለማ መሬት አዘጋጅቶ በማከፋፈል በአርብቶ አደሩ እየለማ ይገኛል፡፡ በርካታ ቁጥር

ያላቸው የአካባቢው ተወላጆች ቤታቸውን በመስራት መኖር የጀመሩ ሲሆን፤ እያንዳንዱ አባወራ/እማወራም የጓሮ መሬት ኖሮት የሚያለማበት ሁኔታ ተመቻችቷል፡፡ ከክልሉ መንግሥት ጋር በመተባበር በደቡብ ኦሞ ዞን ከሚገኙ ስምንት ወረዳዎችና ከጂንካ ከተማ በመጀመሪያ ዙር የተመለመሉ 202 አርብቶ እና አርሶ አደር ስራ ፈላጊ ወጣቶች በግንባታ፣ በአናፂነት፣ በመሰረታዊ ብረት ብየዳ፣ በኤሌክትሪክ መስመር ዝርጋታ፣ በቀለም ቀቢነት እና በለሳኝነት የሙያ መስኮች በጂንካ የኮንስትራክሽንና ኢንዱስትሪያል ኮሌጅ በተግባር የተደገፈ ትምህርት አግኝተው በፕሮጀክቱ በሥራ ላይ እንዲሰማሩ ተደርጓል፡፡ በተመሳሳይ ከኛንጋቶምና ሰላማጎ ወረዳዎች የተውጣጡ በርካታ የቦዲ፣ ሙርሲ፣ ኮንሶና ኛንጋቶም ወጣቶች በጫንጮ የስልጠና ማዕከል በትራክተር ኦፕሬተርነት ስልጠና አግኝተው በሥራ ላይ ተሰማርተዋል፡፡106 የጥቃቅንና አነስተኛ ተቋማት ማኅበራት ተደራጅተውም በተለያዩ ስራዎች እንዲሰማሩ ተደርጓል፡፡

እንግዲህ እነዚህ ህዝብን የሚጠቅሙ ትሩፋቶችን ያስገኘና ወደፊትም የሚያስገኝ የልማት ስራ አክራሪ ኒዮ-ሊበራል ሃይሎቹ ለምን ‘ይቁም’ እንደሚሉ ግልፅ ነው። ምክንያቱም ቀደም ሲል እንደገለፅኩት ፅንፈኞቹ ዓላማቸው ከኒዮ-ሊበራሊዝም ፖለቲካዊ-ኢኮኖሚ እሳቤ ውጪ ሀገሮች እንዳያድጉ ማድረግ እንጂ አንዳችም ዓይነት የሰብዓዊ መብትም ይሁን የአካባቢ ጥበቃ ግብ ስለሌለው ነው። እርግጥም ዓላማቸው ከስያሜያቸው ጋር ግንኙነት ቢኖረው ኖሮ ቀደም ሲል የዘረዘርኳቸውን ምጣኔ ሃብታዊና ማህበራዊ ቱርፋቶችን ያስገኘን ልማታዊ ስራ ለወሬ ያህልም ቢሆን ‘አቁሙ’ ለማለት ባልዳዳቸው ነበር። የህዝቦችን ተጠቃሚነት ለመደፍጠጥ በመሞከር በጠራራ ፀሐይ ባልለፈፉ ነበር። ሽንጣቸውን ገትረው በፀረ-ህዝብነት ባልተሰለፉ ነበር። ህዝቦች ለዘመናት በድህነት ውስጥ እንዲዳክሩና ዘመናዊነት እየናፈቃቸው በኩራዝ ጭላንጭል ብርሃን ውስጥ እንዲመላለሱ በመግለጫቸው ሱባዔ ባልገቡ ነበር።…ግና ሁል ጊዜም ቢሆን በወሬ የፈረሰ የልማት ተግባር የሌለ መሆኑን ላስታውሳቸው እፈልጋለሁ—ለሂዩማን ራይትስ ዎቹ ሌስሌ ሌፍኮ እና ለአሉባልታ ቀማሪ አምሳያቸው።

መቼም እነዚህ ሃይሎች የውሸት ፋብሪካዎች በመሆናቸው እግረ-መንገዳቸውን ጊቤ ሶስትን ሳይጠቅሱ ካለፉ ስቅ ሊላቸው ይችላል። እናም ዛሬም እንደ ትናንቱ ሁሉ በኦሞ ወንዝ ላይ የሚገነባው ሳልሳዊ ጊቤ አካባቢውን ክፉኛ እየጎዳ መሆኑንና ችግሩም በአካባቢው ስነ-ምህዳር እንዲሁም እስከ ኬንያ ድረስ ባሉ ህዝቦች አኗኗር ላይ ከፍተኛ ተፅዕኖ

እንደሚያሳድር ደስኩረዋል። እርግጥ የጊቤ ሶስት የኤሌክሪክ ሃይል ግንባታ በርካታ ጊዜ ምላሽ የተሰጠበት ቢሆንም፤ የፅንፈኞቹ ውሸት ተደጋግሞ እውነት እንዳይመስል አሁንም ጥቂት ስለ ግድቡ ግንባታ መሰረታዊ ሃቆችን መግለፅ የግድ ይላል።

እንደሚታወቀው ጊቤ  ሦስት በቱርካና ሐይቅ ላይም ይሁን በአካባቢው ሥነ - ምህዳር ላይ የሚያስከትለው አንዳችም ጉዳት የለም፡፡ ከዚህ ይልቅ  የግድቡ መሰራት በየጊዜው በመዋዠቅ የሚታወቀውን የቱርካና ሐይቅ ፍሰት ወጥነት እንዲኖረው እንዲሁም ትነቱ እንዲቀነስና የውኃው መጠንም እንዲጨምር ያደርጋል፡፡ እርግጥ የተቋማቱ የፈጠራ ወሬ ከእውነት የራቀ መሆኑን የአፍሪካ ልማት ባንክ ፣ ከስምንት ሀገራት የተውጣጡ የለጋሽ ሀገራት ዲፕሎማቶች እንዲሁም በተባበሩት መንግስታት ድርጅት /ተመድ/ የአካባቢ ጥበቃ ፕሮግራም እ.ኤ.አ. የፌብሩዋሪ 2012 ሪፖርት ብሎም ግድቡን እንዲጎበኙና የቅኝት ስራ እንዲያካሂዱ የተጋበዙት የኬንያ መንግስት ልዑካን ቡድን አባላት ውድቅ አድርገውታል፡፡

የአፍሪካ ልማት ባንክ የቅርብ ጊዜ ሪፖርት ጊቤ ሦስት በኢትዮጵያም ይሁን በኬንያ የግድቡ አካባቢዎች የሚኖሩ ህዝቦችንም ይሁን የተፈጠሮ ሃብትን እንደማይጎዳ አረጋግጧል፡፡ ግድቡን ለመጎብኘት በቦታው የተገኘውና ለበርካታ ቀናት ጉዳዩን ሲያጠና የነበረው የስምንት ለጋሽ ሀገራት አምባሳደሮች ቡድንም የእነ ሂዩማን ራይትስ ዎችን የማያባራ አሉባ “ላም ባልዋለበት ኩበት ለቀማ” መሆኑን አጋልጧል። ከዚህ በተጨማሪም በተመድ የአካባቢ ጥበቃ ፕሮግራም እ.ኤ.አ. የፌብሩዋሪ 2012 ሪፖርቱ እንዳለው፤ በአካባቢው የሚገኙ ሰፋሪዎችን አነጋግሮ ምንም ዓይነት የግዳጅ ሰፈራ አለመከናወኑን እንደተረዳ ይፋ አድርጓል። ግድቡን በተመለከተም የተለየ የአየር ፀባይ ለውጥ እስካልተከሰተ ድረስ የአሞ ወንዝ ውሃ 80 በመቶው ወደ ቱርካና ሃይቅ መፍሰሱን እንደሚቀጥል ገልጿል። የዝናብ መጠኑ ሁኔታ የሚያሰጋ ከሆነ ሃይቁ በየ7 ወራት ጊዜ ውስጥ በ2 ሜትር ዝቅ የማለት ሁኔታ ሊያሳይ እንደሚችልም ጠቁሟል። ይሁንና የዝናቡ መጠን ወጥ ከሆነ በሃይቁ ላይ ምንም ዓይነት ለውጥ እንደማይኖርም አትቷል።

የግድቡ ግንባታ ለሀገራችንና ለኬንያ ህዝቦች ጠቀሜታ ያለው ነው። እነዚህ አክራሪ ኒዮ-ሊበራል ሃይሎች ምንም ዓይነት ትክክለኛ ምስክርነትን የሚሰሙ ባይሆኑም፤ ሃቁ ግን የኬንያ ህዝብ ግድቡ ከሚያመነጨው የኤሌክትሪክ ሃይል ውሰጥ በቂ ሜጋ ዋት ያገኛል። ይህም ሀገሪቷ ለማደግ በምታደርገው ጥረት ላይ የበኩሉን አስተዋፅኦ ማድረጉ አይቀሬ ነው። ምንም እንኳን ተቋማቱ በአንድ ወቅት የተባበሩት መንግስታት ድርጅት ጊቤ ሶስት

በአካባቢው ላይ የሚያደርሰው ተፅዕኖ እሲጣራ ድረስ ግንባታው እንዲቆም እንዲጠይቅ ሊያደርጉ ቢሞክሩም፤ ድርጅቱ ግን የማታ ማታ ቀደም ሲል በጠቀስኩት በአካባቢ ጥበቃ ፕሮግራም መስሪያ ቤቱ አማካኝነት የግድቡ ግንባታ በቱርካና ሃይቅና በኦሞ ወንዝ እንዲሁም በአካባቢው በሚገኙ የኢትዮጵያና በኬንያ ዜጎች ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ የማያሳድር መሆኑን ባደረገው ጥናት ማረጋገጥ ችሏል።

እናም ለእነዚህ ሃይሎች ግድቡ ግንባታ ለሁለቱም ሀገሮች ህዝቦች ያለውን ጠቀሜታ በተመለከተ ከዚህ በላይ ምንም ዓይነት እማኝነት ሊቀርብላቸው አይችልም። ስለሆነም ካደፈጡበት የሐሰት ዋሻ ውስጥ እየመረራቸውም ቢሆን ሊወጡ ይገባል። ውሸት የቱንም ያህል ቢደጋገም እውነትን ሊወልድ ስለማይችል ተግባራቸው ረብ የለሽ መሆኑን ማወቅ ያለባቸው ይመስለኛል። ስለሆነም ሀገራችን የጀመረችውን የዕድገት ጉዞ ይበልጥ እንዲፋጠን በተፈጥሮ ሀብቶቿ ለመጠቀም የማንንም ፈቃድና ይሁንታ የማትጠይቅ ብሎም በውሸት መግለጫዎች ጋጋታ በደቡብ ኦሞም ይሁን በሌሎች አካባቢዎች የህዝቦችን ፍትሐዊ ተጠቃሚነት የሚያረጋግጡ የልማት ፕሮጀክቶችን የምታቆምበት አንዳችም ምክንያት እንደሌለ መገንዘቡ በጄ ነው። ለምን ቢሉ፤ ከድህነት አረንቋ መውጣት የህዝቦቿ የህልውና ጉዳይ ስለሆነ ነው። አበቃሁ።